የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ኤምባሲ ስቶክሆልም
Embassy of the Federal
Democratic Republic of Ethiopia
Stockholm

ቀን 04/10/2017
Date
ቁጥር EEs/1323/2009
No.

# ማስታወቂያ

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ ለገዙ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን

ጉዳዩ፡- የክፍያ ጊዜው የደረሰ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ መቀበል የሚቻልባቸውን ቅርንጫፎች ስለማሳወቅ

በውጭ ምንዛሪ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ ግዥ የፈጸሙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የክፍያ ጊዜው የደረሰን ቦንድ አዲስ አበባ ከሚገኙ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች ወይንም ከኢትዮጰያ ሚሲዮኖች በአካል በመቅረብ ዋናውን የቦንድ ኩፖን በመመለስ ገንዘባቸውን እየተቀበሉ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ ከአዲስ አበባ ውጭ ነዋሪ የሆኑ የቦንድ ግዥ የፈጸሙ ግለሰቦች በየአካባቢአቸው ከሚገኙ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች ገንዘባቸውን መቀበል እንዲችሉ ጥያቄ እያቀረቡ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አሳውቆናል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጥያቄውን ለመመለስ ባደረገው ጥረት በውጭ ምንዛሪ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ ግዥ የፈጸሙና ከአዲስ አበባ ውጭ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አስፋላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት በየአካባቢአቸው ከሚገኙ የባንኩ ቅርንጫፎች ገንዘባቸውን መቀበል እንዲችሉ መወሰኑን እየገለጽን፣ ጉዳዩ የሚመለከታችሁ ሁሉ በዚህ አግባብ መጠቀም እንደምትችሉ እናሳውቃለን።

ከሰላምታ ጋር